# የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር




በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የዲሲና አካባቢው ሀገረ ስብከት የተዘጋጀ

# ዓላማ

የቤተክርስቲያንን ንብረት በአግባቡ ለመጠቀም

- ለሐዋሪያዊ ተልዕኮ
- ለችግረኞች መርጃ

አለመግባባቶችን በፍትህ መንፈሳዊ ለመፍታት

የ ምዕመናን ክርስቲያናዊ ግዴታን ለማሳወቅ

# ጥንተ ታሪክ

“ወንድሞች ሆይ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ” ሐዋ ሥራ 6፡1

# ጥንተ ታሪክ

ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለማዋጣት ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግኩት እናንተ ደግሞ እንደዚሁ አድርጉ 1ኛ ቆሮ 16፥1

# ጥንተ ታሪክ


ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን? ቅዱሳን በዓለም ላይ እንደሚፈርዱ አታውቁምን?

ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን?

ወንድም ወንድሙን ይከሳል ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?

1ኛ ቆሮ 6 1-6

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር
## በየደረጃው የሚገኙት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኢያት አጠቃላይ መዋቅር




በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የዲሲና አካባቢው ህገረ ስብከት የተዘጋጀ

ቅዱስ ሲኖዶስ

የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ
ቤተ ክህነት

የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት

የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት

# የመንበረ ጵጵስና ሀገረ ስብከት ጠቅላላ ጉባኤ አባላት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ | የሀገረ ስብከቱ ስራ አስኪያጅ | ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ ካህናት | ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ ምእመናን | ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የተወከሉ የሰ/ትቤት ወጣቶች |

አንቀጽ 39

# የመንበረ ጵጵስና ሀገረስብከት አስተዳደር ጉባኤ አባላት


የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ መንበር

በሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ካህናት(2-4)

በሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ምእመናን(1-3)

በሀገረ ስብከቱ ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠ የሰንበት ት/ቤት ተወካይ

አንቀጽ 41



የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ
ምክትል ሊቀ መንበር (ካህን/ ምዕመን)
ካህናት (2-4)
የሰንበት ት/ቤት ተወካይ
ምዕመናን (1-3)
የሰበካ ጉባኤ (ሥራ አስፈፃሚ) አባላት

# የሰበካ ጉባኤ ጽሕፈት ቤት

በሰበካ ጉባኤው የሚቋቋም

ዋና ጸሐፊ ይኖረዋል

በአጥቢያው የሚከናወኑ አገልግሎቶችን እየተከታተለ ያሰራል ይሰራል

# ልዩ ልዩ የአገልግሎት ክፍሎች (በሰበካ ጉባኤው የሚቋቋሙ)

- የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል
- የካህናት አገልግሎት ክፍል
- የህንፃ ሥራ ዕድሳትና ጥገና ክፍል
- የስብከተ ወንጌል ክፍል

- የሰንበት ት/ቤት
- የበጎ አድራጎት ክፍል
- ዕቅድና ልማት ክፍል
- ሕግና ሥነ ስርዓት ክፍል
- መዝገብ ቤት(ስታትስቲክስ)

- ሂሳብ ክፍል
- ንብረት(የእቃ ግምጃ ቤት) ክፍል
- የቁጥጥር ክፍል

# የስብከተ ወንጌል ክፍል ሥራና ኃላፊነት



ምዕመናን ስብከተ ወንጌልን እንዲያገኙ ማድረግ

የህትመት ውጤቶችን ማሰራጨት እና መቆጣጠር

ሰባኪያነ ወንጌል የተማሩ  እና የተላኩ መሆናቸውን መከታተል

# የመንፈሳዊ ትምህርት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

ሥርዓተ ትምህርትን የተከተለ መንፈሳዊ ትምህርት መስጠት

ቤተመጻሀፍትን መቋቋም

ለህፃናት መሠረተ ሐይማኖትን፤ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ማስተማር

# የካህናት አገልግሎት ክፍል ሥራና ኃላፊነት

ጸሎተ ቅዳሴው ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲፈጸም

ተገቢውን መስፈርት ያሟሉትን ለድቁና እና ለቅስና ማቅረብ

ሥራቸው ያልታወቀ ክህነታቸው ያልተመርመረ አገልግሎት እንዳይፈጽሙ መከታተል

# ምርጫ አፈፃፀሙና የአግልግሎት ዘመን

አስመራጭ ኮሚቴ(ከ5 - 15) በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣሉ

ዕጩዎችን አጣርተው ያቀርባሉ

ለጠቅላላ ጉባኤው አባላት ስለ እጩዎች ትምህርትና ማብራሪያ ይሠጣሉ

የነባር ጉባኤው የሥራ ዘመን ከማለቁ አንድ ወር በፊት ምርጫው ይካሄዳል

ምርጫው እንደተከናወነ አስመራጭ ኮሚቴው ሥራውን ያቆማል

# የተመራጮች መመዘኛ

“ቃሉን የምታደርጉ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ”

ቃለ ዓዋዲ ገጽ 72

# ካህናት (ቀሳውስት እና ዲያቆናት)

እድሜያቸው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ

ለአስተዳደር ሥራ ተገቢ እና ብቁ የሆኑ መደበኛ አገልጋይ ካህናት

ለቤተክርስቲያን አገልግሎት በጸሎት የሚተጉ ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑ

ግብረገብነታቸው እና ትህትናቸው የተመሰከረላቸው

- *ሥጋዊ ጥቅምና የሥልጣን ሽሚያ ዘረኝነትና ጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ*
- *የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው በወንጀል ተከሰሰው ያልተፈረደባቸው*
- *ከትዕቢት ከተንኮል ከአድማ ከስካር ከፍቅረ ነዋይ የራቁ*

አንቀጽ 10 ንዑስ ቁጥር 2

# ምዕመናን እና ምዕመናት




- ሥጋዊ ጥቅምና የሥልጣን ሽሚያ ዘረኝነትና ጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰባቸውን ያዛባዋል ተብለው የማይጠረጠሩ
- የገንዘብ ጉድለት ያልተገኘባቸው በወንጀል ተከሰሰው ያልተፈረደባቸው
- ከትዕቢት ከተንኮል ከአድማ ከስካር ከፍቅረ ነዋይ የራቁ

አንቀጽ 10 ንዑስ ቁጥር 2

# ስለ ጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣን

- አስመራጭ ኮሚቴውን ይሰይማል
- የሥራ ክንውን እና ኦዲት ሪፖርት ይሰማል
- የሰባካ ጉባኤ አባላትን ይመርጣል
- አመታዊ በጀትን መርምሮ እንዲፈቀድ ለሊቀ ጳጳሱ ያስተላልፋል
- በሰበካ ጉባኤ ተመርጠው የሚቀርቡትን የክፍል ሐላፊዎች ያፀድቃል
- ተጠሪነቱ ለወረዳው ቤተ ክህነት(ለሀገረ ስብከቱ) ይሆናል

አንቀጽ 8

# ምርጫ ስለማጽደቅ

የሰበካ ጉባኤ አባላት በሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ

ሥራ ከተጀመረ በኋላ ለሚፈጠር ችግር በሀገረ ስብከቱ ጉባኤ ተጠንቶ ሊሻር ይቻላል

የአግልግሎት ክፍል ኃላፊዎች ምርጫ በጠቅላላ ጉባኤው ይጸድቃል

# የአገልግሎት ዘመን

- በአንቀጽ 11 ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ሦስት አመት
- በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ብቻ ስለመመረጥ
- አንዳንድ የምርጫ ጊዜ እያሳለፉ ስለመመረጥ

# ምን እናድርግ? ሐዋ ሥራ 2:37

